# የታካሚ መረጃ:- ሞልኑፒራቪር (MOLNUPIRAVIR)

ሞልኑፒራቪር (Molnupiravir) በ COVID-19 ለከባድ ሕመም ከፍተኛ ተጋላጭ ለሆኑ አዋቂዎች ሆስፒታል መተኛትን ወይም ሞትን **ሊከላከል ይችላል**። የ COVID-19 ምልክቶች መታየት በጀመሩ በ **5** ቀናት **ውስጥ መወሰድ** አለበት።



## ሞልኑፒራቪር (Molnupiravir) ምንድን ነው?

**ሞልኑፒራቪር (Molnupiravir) ከቀላል እስከ መካከለኛ የ COVID-19 ህመምን ለማከም የሚያገለግል አዲስ መድኃኒት ሲሆን ለሚከተሉት አዋቂዎች(ዕድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ ለሆነ)** ያገለግላል:-

- የ COVID-19 ቫይራል ምርመራፖዘቲቭ **የምርመራ ውጤት** ላላቸው
- በሆስፒታል መተኛትን እና ሞትን ጨምሮ *ለከባድ የ COVID-19 ከፍተኛ ተጋላጭነት ያላቸው* እና ሌሎች የ COVID-19 ህክምና አማራጮችን የማያገኙ ወይም አማራጮቹ ትክክለኛ ወይም ተገቢ ላልሆኑላቸው።

**ሞልኑፒራቪር (Molnupiravir)** ለ **5** ቀናት በአፍ (እንክብሎችን በመዋጥ) የሚወሰድ ፀረ-ቫይረስ መድሃኒት ነው። የህመም ምልክቶች መቀነስ ቢያሳዩም እንኳን፣ የሕክምናው ሂደት (መድሃኒቱን መውሰዱ) መጠናቀቅ አለበት።

የአሜሪካ የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር (FDA) ሞልኑፒራቪር (Molnupiravir) በ COVID-19 ወረርሽኝ ወቅት እንዲገኝ ለማድረግ የአደጋ ጊዜ አጠቃቀም ፈቃድን (EUA) ሰጥቷል። **ሞልኑፒራቪር (Molnupiravir)** በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በ FDA የጸደቀ መድሃኒት አይደለም።



## የሚከተሉት ሁኔታዎች ካሉብዎት ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ይናገሩ:-

- **ነፍሰ ጡር** ከሆኑ፣ ወደፊት ነፍሰ ጡር ሊሆኑ የሚችሉ ከሆነ፣ ወይም ወደፊት ሊያረግዙ ከሚችሉ አጋሮች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እያደረጉ ከሆነ።
- የትኛውም ዓይነት **አለርጂዎች ካሉብዎት**
- ልጅ **እያጠቡ ከሆነ** ወይም ለማጥባት አቅደው ከሆነ
- የትኛውንም አይነት **ከባድ ህመሞች ካሉብዎት**
- የትኛውንም አይነት መድኃኒቶች **እየወሰዱ ከሆነ** (በሃኪም የታዘዙ፣ ካለማዘዣ የሚዋሰዷቸው፣ ቫይታሚኖች ወይም የእፅዋት ውጤቶች)

## ሞልኑፒራቪር (Molnupiravir) የጎንዮሽ ጉዳቶች አሉት?



- **ሞልኑፒራቪር (Molnupiravir)** ባልተወለዱ ሕፃናት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል (በእንስሳት ላይ ከተደረጉ ጥናቶች በተገኘ መረጃ ላይ በመመርኮዝ)
- ሞልኑፒራቪር (Molnupiravir) በሚወሰዱ **ሰዎች ላይ የአለርጂ አጸፋዊ ምላሾች (allergic reactions) ሊከሰቱ ይችላሉ።**
- በጣም የተለመዱት የጎንዮሽ ጉዳቶቹ የሚከተሉት ናቸው:-
  - ተቅማጥ
  - ማቅለሽለሽ
  - ራስን ማዞር



## ሞልኑፒራቪርን (Molnupiravir) የት ማግኘት እችላለሁ?

የሞልኑፒራቪር (Molnupiravir) መገኛ ቦታዎች በ VDH የ COVID-19 ሕክምና ጠቋሚ መሳሪያ ላይ ይገኛሉ። **ሊንኩ በቨርጂኒያ ውስጥ ህብረተሰቡ እና አቅራቢዎች የህክምና ጣቢያዎችን ወይም ቦታዎችን እንዲያገኙ የሚያስችል በ VDH ድረ-ገጽ ላይ በድረ-ገጽ የተሳሰረ ካርታ (interactive map) ነው:-**
*https://www.vdh.virginia.gov/mabs/covid-19-treatment-locator/*

**ለሁሉም ሊገኙ ለሚችሉ መፈውሦች/ሕክምናዎች የሐኪም ማዘዣ ያስፈልጋል።**

VIRGINIA'S HEALTH IS IN OUR HANDS.
Do your part, stop the spread.

ስለ COVID-19 ሕክምናዎች ተጨማሪ መረጃ በ *https://www.vdh.virginia.gov/coronavirus ላይ ማግኘት ይችላሉ።*

VDH VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH